በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት
የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

የኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች የሥራ አመራር ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የወጪ ሂሳብ

1.1 ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ፡

1.1.1 ግኝት

ሰኔ 2/2002 የወጣው የፌዴራል የመንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት እንዲሁም ታህሳስ 1/2008 በተሻሻለው አዋጅ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀፅ 1 ከብር 200,000.00 በላይ የሆኑ ግዥዎች በግልጽ ጨረታ መገዛት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

ለላብራቶሪ ዕቃዎች ግዥ-----------------	ብር	4,699,924.78
ለፓርቲሽን ስራ ---------------------------	ብር	1,755,381.18
ለአበባ ማስቀመጫ --------------------------	ብር	334,569.27

በግልጽ ጨረታ ሊገዙ ለሚገባቸው ዕቃዎች በመመሪያው መሠረት ሌሎች አቅራቢዎች በግዢ እንዲሳተፉ ማስታወቂያ ሳይወጣ አለአግባብ በውስን ጨረታ በጠቅላላ የብር 6,789,875.23 ግዢ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል፡፡

1.1.2 ሥጋት

መንግስት ዋጋን በማወዳደር ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ አስፈላጊነታቸው ታምኖበት በመንግስት የወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎችን የሚጥስ በመሆኑ ለብልሹ አሰራር መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች ሲፈጸሙ በመንግስት የወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ ተደርገው ግልጽ ጨረታ ወጥቶ በማወዳደር ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችለውን በመምረጥ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጸም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.1.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

በግልፅ ጨረታ መከናወን እንዳለበት የምንረዳው ቢሆንም እንደሚታወቀው ተቋማችን አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችን በአብዛኛው ቅጥር ያከናወነውና ወደ ሥራ ያስማራው ከሚያዚያ ወር ጀምሮ በመሆኑና በዚህ ሂደትም አስፈላጊ የሆኑ የላብራቶሪ ዕቃዎችን የመለየትና ስፔስፊኬሽን የሚያዘጋጁ ቴክኒካል ኮሚቴዎችን አዋቅሮ ወደ ሥራ ለመግባት ጊዜን የሚጠይቅ ተግባር ከመሆኑ አንፃር በግልፅ ጨረታ ለመጠቀም የበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ የተቃረበ በመሆኑ ምክንያት በአለን ውስን ቀሪ ጊዜ ወደ ውስን ጨረታ ለመግባት የተገደድን በመሆኑ ነው፡፡

የፓርቲሽን ሥራውም የላብራቶሪ ዕቃዎች ተገዝተው ሥራ ለማስጀመር አስፈላጊውን የሥራ ማከናወኛ የማደራጀት ሥራ የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር የተከናወነ መሆኑን እየገለፅን ለወደፊቱ መመሪያና ደንቡ በሚፈቅደው አግባብና በተሰጠን አስተያየት መሠረት የምንተገብር መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

1.2 <u>ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

1.2.1 <u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ተ.ቁ 2 አገልግሎቱ በተፈለገው ስፔስፊኬሽን መሠረት መቅረቡን ወይም አገልግሎቱ መሰጠቱን ሲረጋገጥ እና እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ተ.ቁ 2/ለ መሰረት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳአለበት ታዟል፡፡ ሆኖም በሂሳብ መደብ 6223 በተለያየ የወጪ ቫውቸር በድምሩ ብር **15,703,786.50** ለምርምርና ስርፀት ለተለያዩ ዩንቨርሲቲዎች እና የትምህርት ተቋማት በባንክ ዝውውር የተላለፈ ሂሳብ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አለአግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል፡፡

1.2.2 ሥጋት

ማንኛውም ሂሳብ የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃ መኖሩ ሳይረጋገጥ እንዲመዘገብ ማድረግ የገንዘብ ጥፋትና ጉድለት እንዲፈጸም ሊገፋፉ ይችላል፡፡

1.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሊመዘገብ እና ማስረጃ ሲቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጸም ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱ ስራ አመራር ለምርምር እና ስርፀት ማስፈፀሚያ መስፈርት በማዘጋጀት በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲውል ሊያደረግ ይገባል፡፡

1.2.4 የሥራ አመራር ምላሽ

በሀገር አቀፍ ደረጃ ችግር ፈች የሆኑ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርምሮችን ለሚያከናውኑ ተመራማሪዎች (በአብዛኛዉ ሳይንቲስቶች) በሚሰሩበት ተቋማት (ዩንቨርስቲዎች) በኩል የተሰጠ ድጋፍ በመሆኑና ከበጀት ውስንነት አንፃር በአንድ ጊዜ ለመክፈል አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት በቴክኒካል ኮሚቴ ግምገማ አማካይነት ታይቶ ቀሪዉ ገንዘብ በየዓመቱ ከገ/ኢ/ት/ሚ/ር በሚመደብልን በጀት አማካይነት ለምርምርና ስርፀት ሥራ አገልግሎት በመሆኑ እንደሌሎች ግዥና አገልግሎት ክፍያዎች በተሰብሳቢ መያዙ አስቸጋሪ ስለሚሆን፤ የዓመቱም ወጭ በመሆኑና ተመላሽም ስለማይሆን በዚህ አግባብ የታየ ነው፤ ሆኖም ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እየገልፃለን፣ ይህንኑ ለማድረግ ከገ/ኢ/ት/ሚ/ር ጋር ውይይት መጀመሩን እናስታውቃለን፡፡

2. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

2.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር አንድ ላይ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ለኢንስቲትዩቱ በበጀት ዓመቱ ከተመደበው በጀት ውስጥ በዋና ዋና በጀት አርዕስቶች ከ10% በላይ ያልተሠራበት በጀት ለመኖሩ ማጣራት ሲደረግ ለመደበኛ በጀት ከተደለደለው ብር 2,706,158.35 እና ለካፒታል በጀት ከተደለደለው ደግሞ ብር 6,808,255.51 በድምሩ ብር 9,514,413.86 ስራ ላይ ሳይውል ተገኝቷል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል፡፡

2.2 ስጋት

የተፈቀደው በጀት በዕቅድና በፕሮግራም መሠረት ሥራ ላይ ካልዋለ አገሪቱ ያላት ውስን በጀት ለሌሎች ሥራዎች እንዳይውል ሊያደርግ እንዲሁም የበጀት እቅድ ዝግጅቱ በቂ ጥናት ያልተደረገበት መሆኑን ሊያመለክት ይችላል፡፡

2.3 የማሻሻያ ሃሣብ

ኢንስቲትዩቱ በጀትን በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችል ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ስለሆነም ለወደፊቱ በበጀት ጥያቄ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.4 የሥራ አመራር ምላሽ

በሂሳብ መደብ 6100 ኢንስቲትዩቱ አዲስ የተቋቋመ ከመሆኑ አንፃር ከገ/ኢ/ት/ሚ/ር የዓመቱ በጀት ዘግይቶ የተፈቀደ በመሆኑ የሠራተኞች ቅጥርም ከመጋቢት ወር አጋማሽ በኃላ የጀመሩ በመሆኑ ምክንያት የተመደበውን በጀት ሙሉ በሙሉ መጠቀም ባለመቻላችን ነው፡፡ በሂሳብ መደብ 6200 ከአቅራቢዎች የሚፈለገው እቃ ሙሉ በሙሉ ሊገኝ ባለመቻሉ፣ ተቋማችው አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ የተገባው ከሠራተኞች ቅጥር በኂላ በመሆኑ፣ የዕዳት እቃዎች በማዕቀፍ ግዥ ዝርዝር ውስጥ ሊገኝ ባለመቻሉ

በዋጋ ለቀማ የተወሰነ ብቻ በመገዛቱ፣ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ለትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ተደጋጋሚ የገንዘብ ጥያቄ(ካሽ ፍሎው) ቢያቀርቡም በምዝገባ ስህተት ምክንያት በወቅቱ ምላሽ ባለማግኘታቸው እና በጊዜው የመብራት እና የውሀ ፍጆታ የሂሳብ ቢል ባለመምጣቱ በሚፈለገው መጠን በጀቱን ሥራ ላይ ለማዋል ባለመቻሉ ምክንያት ተራፊ የሆነ ነው፡፡

3. ንብረት አስተዳደር

3.1 ግኝት

በመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 65.5 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ተ.ቁ 1/መ፣ሠ እና ረ መሰረት ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ እየተቆጠረ ከወጪ ቀሪው መመዛዘን፣ ለቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር መስጠት እና የንብረት መዝገብ ወቅታዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ፣

- በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የንብረት ም□□ብ የማይከናወን በመሆኑ ከመዝገብ /ሰቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር ያልተደረገ መሆኑ፤
- ለቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3.2 ሥጋት

በንብረት አያያዝ ላይ ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ የንብረት ጥፋትና ጉድለት ቢከሰት በወቅቱ ላይደረስበት ይችላል፡፡

3.3 የማሻሻያ ሀሳብ

የንብረት ገቢ እና ወጪ ምዝገባ በወቅቱ እንዲከናወን እና ለቋሚ ንብረቶች የንብረት መለያ ቁጥር እንዲሰጥ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የዕቃ ቆጠራ ከመዝገብ /ሰቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር ተደርጎ ውጤቱ ለበላይ ኃላፊ ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

በ2009 ዓመታዊ ንብረት ቆጠራ አካሂደናል፡፡ ንብረቶቹም ሲቆጠሩ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 በማመሳከር ምን ያህል ንብረት እንዳሉ ለማወቅ ችለናል፡፡ እነዚህንም ንብረቶች ወደ ስቶክ ካርድ ለመመዝገብ የተቆጠሩትን ንብረቶች ተገቢውን መለያ ቁጥር እየሰጠን እንገኛለን፡፡

4. <u>ልዩ ልዩ</u>

4.1 <u>የውስጥ ኦዲት</u>

4.1.1 <u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግሥት የዉስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 8/2 መሰረት የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ መመደብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩት በውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት መዋቅር መሠረት አንድ የኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ፣አንድ ኦዲት ቡድን መሪ፤ አንድ ከፍተኛ ኦዲተር እና አንድ ሴክሬታሪ ሊኖረው እንደሚገባ የተገለጸ ቢሆንም በኢንስቲትዩቱ የሚገኘው አንድ ከፍተኛ ኦዲተር ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 በክፍል 5 ተራ ቁጥር 3 የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ማቅረቢያ የግዜ ሰሌዳ 1ኛ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30/2009፣ የሁለተኛ ሩብ አመት እስከ ጥር 30፣ የሶስተኛ ሩብ አመት እስከ ሚያዚያ 30 እንዲሁም የአራተኛ ሩብ አመት እስከ ነሃሴ 15 ድረስ መሆን ይኖርበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የሶስተኛ ሩብ አመት ሪፖርት እና የአራተኛ ሩብ አመት ሪፖርት እሰከ 22/02/2010 ድረስ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.1.2 <u>ሥጋት</u>

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ የተፈቀደለት የሰው ኃይል ባለመሟላቱ ኦዲቱ በወቅቱ እና በአግባቡ እንዳያከናወን ምክንያት ይሆናል፡፡

4.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የውስጥ ኦዲት ክፍሉን የሰው ኃይል በማሟላት እና በማጠናከር የኢንስቲትዩቱ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እንዲጠናከር ሊደረግ ይገባል፡፡

4.1.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

ኢንስቲትዩታችን አዲስ የተቋቋመ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የቅድመ ሥራዎች ከተጠናቀቁ በኃላ የሠራተኞች ቅጥር የተከናወነው ከመጋቢት ወር አጋማሽና በሚያዚያ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ የኦዲት ባለሙያ ቅጥርም ከገ/ኢ/ት/ሚ/ር ይሁንታ ማግኘት ያለበት ስለሆነ በዚህ ምክንያት ቅጥሩ ሊዘገይ የቻለ መሆኑን እየገለፅን የውስጥ ኦዲት ክፍሉን የማጠናከር ሥራ በተሰጠን አስተያየት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡

4.2 የ<u>ስራ ክፍፍል የሌለ ስለመሆኑ</u>

4.2.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 8 ቁጥር 1 ሀ ላይ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች መካከል ሊኖር የሚገባውን መዋቅራዊ ግንኙነቶች በመመስረት ሊነጣጠሉ የሚገባቸውን ሥራዎችና ኃላፊነቶች በተለያዩ ሰዎች ተከፋፍለው እና ተለይተው እንዲሰሩ የሚያስችል ስልት መዘረጋት እንዳለበት እና ስራዎች በሚመለከተው ባለሙያ ብቻ መከናወን እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ሆኖም በኢንስቲትዩቱ ንብረት ገቢ እና ወጪ የማድረግ ተግባርና የንብረት መጠበቅ ኃላፊነት በአንድ የሰው ሀይል ተደርቦ የሚሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.2.2 <u>ሥጋት</u>

ንብረት ምዝገባ የሚያከናውን ሠራተኛ የንብረት መጠበቅ ተግባር እንዲያከናውን መመደብ ለመንግሥት ሀብትና ንብረት ጥንቃቄ የማይደረግ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ ለምዝበራ መንገድ ይከፍታል፡፡

4.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

እንደ ሰራው ባህሪ ሊነጣጠሉ የሚገባቸው ሥራዎችና ኃላፊነቶች በተለያዩ ሰዎች ተከፋፍለው እና ተለይተው እንዲሰሩ የስራ አመራሩ ተገቢ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

4.2.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

ቀደም ሲል በጥናቱ ወቅት ያልታየ ክፍተት በመሆኑ ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር ጋር በጉዳዩ ላይ እየተነጋገርንበት በመሆኑ በተሰጠው አስተያየት መሠረት በቀጣይ ተገቢውን የሰው ኃይል የምናሟላ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

4.3 <u>የስጋት ምንጮች ዳሰሳ አለመከናወኑ</u>

4.3.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 በክፍል 4 አንቀፅ 13 የመንግሥት መ/ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ በመለየት የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማኬሂድ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እና ሥጋቶችን እንደየክብደታቸዉ በመለየት ሥጋቶችን በከፊል እንዲሁም ሙሉ በሙሉ የሚቀነስበት የስጋት ምንጮች ዳሰሳ (Risk assessment Policy) አለማዘጋጀቱ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

4.3.2 <u>ስጋት</u>

የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ ካልተቀመጠ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በወቅቱ ለማስተካከል ወይም እርምጃ ለመወሰድ አያስችልም፡፡

4.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በመመሪያው መሰረት የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ሊዘገጅና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት ቅድመ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

4.4.4 የሥራ አመራር ምላሽ

ኢንስቲትዩታችን አዲስ ከመሆኑ አንፃር ለወደፊቱ ሰፊ የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ማከናወን የሚጠበቅበት ቢሆንም በእስከአሁን እንቅስቃሴአችን በህግ አገልግሎትና በሥነ ምግባር ክትትል ዳይሬክቶሬት በኩል መሠረታዊ በሆኑ የህግ ፅንሰ ሀሳብና በስነምግባር አተገባበር ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተከናዉኗል፡፡

በተጨማሪም መልካም የሥራ ግንኙነትን ለመፍጠርና በአሰራር ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ የዲስፕሊንና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተቋቁመው እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል፡ በቀጣይም የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን በመለየትና ሌሎችንም የሥጋት ተጋላጭነት በመዳሰስ አግባብ ያለው የማስተካከያ እርምጃዎች እንወስዳለን፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡:

አባሪ 1
ግልፅ ጨረታ ሳይወጣ የተፈፀመ ግዢ

ተ.ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የወጪ ምክንያት	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	29/10/2009	044139	ፓርትሽን የተሰራበት	6244	1,755,381.18
2	28/10/2009	044119	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	1,094,794.94
3	29/10/2009	044135	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	1,140,000.00
4	28/10/2009	044129	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	1,034,699.84
5	28/10/2009	044121	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	710,000.00
6	910/2009	044087	አበባ ማስቀመጫ የተገዛበት	6314	334,569.27
7	29/10/2009	044141	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	257,929.96
8	28/10/2009	044120	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	245,700.00
9	28/10/2009	044127	የላብራቶሪ እቃ የተገዛበት	6313	216,800.04
			ድምር		6,789,875.23

አባሪ 2

<u>ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

ተ.ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	ገንዘቡን የተቀበለው ዩኒቨርሲቲ/ተቋም	የገንዘብ መጠን
1	20/10/2009	044096	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	1,485,000.00
2	20/10/2009	044097	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	1,440,150.00
3	20/ 0/2009	044099	ደብረብርሃ ዩኑቨርስቲ	1,420,419.00
4	22/10/2009	044105	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	1,363,200.00
5	30/10/2009	044155	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	1,125,000.00
6	30/10/2009	044148	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	1,072,362.00
7	30/10/2009	044151	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	1,009,470.00
8	30/10/2009	044149	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	996,600.00
9	30/10/2009	044147	ኢ.ዩ. ኮሌጅ ፎፍ ቨተርነሪ መዲስን ኤንደ አግሪካቸር	899,168.00
10	20/10/2009	044092	አርመር ሃስን ሪሰርች ኢንስቲቱት	898,182.00
11	30/10/2009	044152	ኢትዮጵያን ኢንስቲቱ ኦፍ አግሪካለቸር ሪሰርች	855,000.00
12	30/10/2009	044146	ኢ.ዩ. ኮሌጅ ፎፍ ቨተርነሪ መዲስን ኤንደ አግሪካቸር	847,886.00
13	20/10/2009	044094	መቀሌ የኒቨርስቲ ቨተርነሪ	686,452.00
14	20/10/2009	044098	ጎንደር ዩንቨርሲቲ	644,664.00
15	20/10/2009	044093	ሆፐ ኮሌጅ ፎፍ ሳይንስ ኤንደ ቴክኖሎጂ	385,970.50
16	20/10/2009	044095	አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ	329,993.00
17	30/10/2009	044150	ኢትዮጵያ ሌዘር ኢንደስተሪ ዲቨሎፕመንተ ኢንስትዩቲት	244,270.00
			ድምር	**15,703,786.50**

አባሪ 3 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

መደበኛ በጀት

ተራ ቁ.	የሂሣብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	የበጀት ዓመቱ ወጪ	ያልተሰራበት በጀት	በመቶኛ %
1	6111	3,970,937.00	2,842,766.23	1,128,170.77	28%
2	6114	40,000.00	34,960.16	5,039.84	13%
3	6131	638,000.00	295,544.99	342,455.01	54%
4	6212	450,000.00	205,748.15	244,251.85	54%
5	6213	780,000.00	614,533.24	165,466.76	21%
6	6215	50,000.00	7,061.00	42,939.00	86%
7	6217	420,000.00	245,021.59	174,978.41	42%
8	6218	180,000.00	68,438.52	111,561.48	62%
9	6219	100,000.00	6,936.04	93,063.96	93%
10	6223	70,000.00	8,275.20	61,724.80	88%
11	6231	455,000.00	340,739.67	114,260.33	25%
12	6244	100,000.00	62,285.78	37,714.22	38%
13	6254	85,000.00	68,198.71	16,801.29	20%
14	6257	115,000.00	76,153.19	38,846.81	34%
15	6258	410,000.00	355,763.85	54,236.15	13%
16	6259	85,000.00	10,352.33	74,647.67	88%
	ድምር	**7,948,937.00**	**5,242,778.65**	**2,706,158.35**	**34%**

ካፒታል በጀት

ተራ. ቁጥር	የሂሣብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	የበጀት ዓመቱ ወጪ	ያልተሰራበት በጀት	በመቶኛ %
1	6244	5,000,000.00	1,755,381.17	3,244,618.83	65%
2	6313	12,000,000.00	8,436,363.32	3,563,636.68	30%
	ድምር	**17,000,000.00**	**10,191,744.49**	**6,808,255.51**	**40%**